የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

ሆሳዕና 2ኛ ዓመት ቁጥር
መስከረም 23 ቀን 2017 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ

Hossana 2nd Year No
Oct. 3 /2024

ደንብ ቁጥር 20/2017 ዓ.ም

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር ደንብ

መ ግ ቢ ያ

የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የክልሉ ታክሶች የሚመሩበት ራሱን የቻለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 8/2016 የወጣ በመሆኑ፣

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግና ለግብር ከፋዩ የግብር ግዴታውን በተሟላ ሁኔታ ለማሳወቅ የሚያስችል ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ማስፈፀሚያ ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ፣

አዋጁን ለማስፈፀም ግልጽ መሆን የሚገባቸውን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ለይቶ በማመልከት በአፈፃፀም ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል በመሆኑ፣

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ሕገ- መንግስት አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ 6 እና የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም፤ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ ጠቅላላ</u>

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ **"የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ክልል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 20/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. **"አዋጅ"** ማለት የክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 8/2016 ነው፤
   2. በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጐች እንደአግባብነቱ በአዋጁ ወይም በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 10/2016 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   ይህ ደንብ በክልሉና ከክልሉ ውጪ ባሉ የክልሉን ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለባቸው አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

4. ሚስጥራዊ መረጃ ስለመስጠት

የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 8(2) እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ሚስጥራዊ ሰነድ ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ጥያቄው በጽሑፍ ለቢሮ ኃላፊ ወይም እሱ ለሚወክለው ሰው ሲቀርብ እና ሲፈቀድ ብቻ ነው።

ክፍል ሦስት

ስለምዝገባ

5. የማንነት የሰነድ ማስረጃ

1. ማንኛውም ግለሰብ ከሚያቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ከሚከተሉት አንዱን የማንነት የሰነድ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
   ሀ) ወቅታዊ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ገፅ የተረጋገጠ ቅጂ፣ ወይም
   ለ) የግለሰቡ ወቅታዊ የኢትዮጵያ የመንጃ ፈቃድ የተረጋገጠ ቅጂ፣ ወይም
   ሐ) የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ ኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ ገጽ የተረጋገጠ ቅጂ፣ ወይም
   መ) የግለሰቡ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ቅጂ፤
   ሠ እንደአስፈላጊነቱ ዲጅታል ብሔራዊ መታወቂያ
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ቢሮው አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሌላ ማንኛውም ማስረጃ እንዲያቀርብለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል።
3. በኩባንያ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኩባንያው የተቋቋመበትን ወይም የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ ማቅረብ አለበት።
4. በሽርክና ማህበር የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከሽርክና ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።
5. በሌላ ማንኛውም ድርጅት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከድርጅቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማንኛውም የመመስረቻ ወይም ማቋቋሚያ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

6. **አካላዊ የማንነት መረጃ**

1. ለግለሰብ ምዝገባ ዓላማ ቢሮ፡-

ሀ) የግለሰቡን ትክክለኛ ማንነት ለማረጋገጥ፣ወይም

ለ) የማንነት ስርቆትን ወይም ማጭበርበርን ለመከላከል፣

አመልካቹን ግለሰብ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ከግለሰብ ጋር በተገናኘ **"የማንነት አካላዊ መረጃ"** ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) የፊት ገጽታ መለያ፣

ለ) የጣት አሻራ መለያ፣

ሐ) የድምጽ መለያ፣

መ) የዓይን ክፍሎች(ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ፣

ክፍል አራት

<u>የታክስ እንደራሴዎች</u>

7. **ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ**

1. ለአዋጁ አፈፃፀም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 4(4) መሠረት በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት **"ወኪል"** ተብሎ በሚጠራ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውነው የንግድ ሥራ ወኪሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የታክስ እንደራሴ ተደርጎ ይቆጠራል።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደታክስ እንደራሴ የሚቆጠር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወኪል በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 16(2) መሠረት ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ ከሆነ ሌላ ማንኛውም ሰው ተጨማሪ እንደተሰየመ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል።

ክፍል አምስት

የከባድ ችግር ሁኔታዎች

8. **የታክስ ምህረት ገደብ**

1. የፋይናንስ ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 51 መሠረት የሚሰጠው የታክስ ምህረት የገንዘብ ጣሪያ 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ብር ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 1,000,000(አንድ ሚሊዮን) በላይ የሆነ የታክስ ምህረት ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ክፍል ስድስት

ማስታወቂያዎች እና የታክስ ክፍያ

9. **የሰነዶች አቀራረብ እና የታክስ አከፋፈል ሥርዓት**

በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በሚከተለው አኳኋን ለቢሮ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፡፡

1. የአዋጁ አንቀጽ 82(2) ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በማስተላለፍ ወይም የአዋጁን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ቢሮ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ክፍያ መፈጸም፣ ወይም
2. በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በአካል በማቅረብ ወይም በፖስታ ለቢሮ በመላክ፤

10. **ገቢ ማስታወቂያ ስፍራ**

1. የገቢ ማስታወቂያ የሚቀርበው ለቢሮው ይሆናል፡፡
2. ከአንድ በላይ የሆነ የንግድ ሥራ ያለው ግብር ከፋይ ገቢውን ማስታወቅ የሚገባው የንግድ ሥራው ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባለው የገቢዎች መስሪያ ቤት ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ ዞን፣ልዩ ወረዳ፣ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የንግድ ትርፍ ግብሩን መክፈል ያለበት የንግድ ሥራውን በሚያከናውንበት ዞን፣ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መስሪያ ቤት ነው፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ Central Ethiopia Region State Justice Bureau
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት Central Ethiopia Regional State Office of the President

ክፍል ሰባት

የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

ምዕራፍ አንድ

የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ የአባላት አመዳደብና የአሠራር ሥርዓት

11. የኮሚሽኑ አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 86(1) መሠረት የተቋቋመው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በክልል ማዕከል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣በከተማ አስተዳደሮች እና እንደ አስፈላጊነቱ በወረዳ ደረጃ የራሱ ጽ/ቤት ያለው ሆኖ በዚህ ደንብ ተደራጅቷል፡፡
2. በክልል ማዕከል ደረጃ የተደራጀው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳደሩ ሲሆን በዞን ደረጃ ለዞኑ/በልዩ ወረዳ ደረጃ ለዋና አስተዳዳሪ፣ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለከንቲባ እና በወረዳ ደረጃ ለወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪ ይሆናል፡፡
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12(2) ላይ የተመለከቱ የኮሚሽኑ ቋሚ አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተገለጸው ኮሚሽኑ ተጠሪ በሆነበት አስተዳደር አካል የሚመደቡ ይሆናል፡፡
4. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12(2)ሀ ላይ የተመለከቱ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ኮሚሽኑ ተጠሪ ለሆነበት የአስተዳደር አካል ሲሆን ሌሎች የኮሚሽኑ አባላት ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

12.. የኮሚሽኑ አባላት ብዛትና ስብጥር

1. በክልል፣ በዞን፣በልዩ ወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ የተደራጀው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ድምጽ የሚሰጡ አምስት ቋሚ አባላት እና እንደየጉዳዮች ባህሪ የሚቀየርና ድምጽ የሚሰጥ አንድ ተለዋጭ አባል በድምሩ ስድስት አባላት ይኖሩታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቋሚ የኮሚሽኑ አባላት ስብጥር፡-
   ሀ) በአስተዳደር አካል መዋቅር የሚመደብ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ሆኖ የሚያገለግል አንድ ሰው፤

ለ) ከፍትህ ቢሮ መዋቅር የሚመደብ እና የኮሚሽኑ ፀሐፊ ሆኖ የሚያገለግል አንድ ሰው፤

ሐ) ከፋይናንስ ቢሮ መዋቅር የሚመደብ እና የኮሚሽኑ አባል ሆኖ የሚያገለግል አንድ ሰው፤

መ) ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መዋቅር የሚመደብ እና የኮሚሽኑ አባል ሆኖ የሚያገለግል አንድ ሰው፤

ሠ) የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤትን ወክሎ የሚመደብ እና የኮሚሽኑ አባል ሆኖ የሚያገለግል አንድ ሰው፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደየሚቀርቡ የግብር ይግባኝ ጉዳዮች ባህሪ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ አግባብነት ካለው አካል የሚመደብ ድምጽ የሚሰጥ አንድ ተለዋጭ አባል ሊመረጥ ይችላል፡፡

13. <u>የኮሚሽኑ አባል የአገልግሎት ዘመን</u>

ቋሚ የሆነ የኮሚሽኑ አባል የአገልግሎት ጊዜ ለሦስት ዓመት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ለሁለተኛ ጊዜ ሊመደብ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ለሦስተኛ ጊዜ ሊመደብ አይችልም፡፡

14. <u>ቋሚ የኮሚሽኑ አባላት የምደባ መስፈርት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12(2) መሠረት ከየተቋማት የሚመደብ ቋሚ የኮሚሽኑ አባል ቀጥሎ የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

ሀ) ከአስተዳዳር አካል መዋቅር የሚመደብ ሰው በአመራር ሥራ በቂ ልምድ ያለው፤

ለ) ከፍትህ ቢሮ መዋቅር የሚመደብ ሰው በታክስ ሕጎች ላይ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው ሰው፤

ሐ) ከፋይናንስ ቢሮ መዋቅር የሚመደብ ሰው በታክስ የሂሳብ ሥራ ላይ ልምድ ያለው ሰው፤

መ) ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መዋቅር የሚመደብ ሰው በንግድ የአሠራር ሥርዓቶችና ሕጎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ልምድ ያለው ሰው፤

ሠ) የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤትን በመወከል የሚመደብ ሰው የም/ቤቱ ፕሬዝዳንት ወይም የአመራር አካል የሆነ ሰው፤

2. የሚከተሉት ሰዎች የኮሚሽኑ አባላት ሆነው ሊመደቡ አይችሉም:-

ሀ) በታክስ ሠራተኛነት በማገልገል ላይ ያለ ሰው ወይም የታክስ ሠራተኛነቱን ከተወ ሁለት ዓመት ያልሞላው ሰው፤

ለ) ከታክስ ማጭበርበር ወይም ስወራ ጋር በተገናኘ በታክስ ሕግ መሠረት ቅጣት የተጣለበት ወይም በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው፤

ሐ) በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው፤

መ) በዲስፕሊን ጉዳይ ተከሶ ጥፋተኛ የተባለና በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ መሠረት የጥፋተኝነት ሪከርድ ጊዜውን ያልጨረሰ፤

ሠ) በንግድ የተሰማራ ሆኖ እዳውን ያልከፈለ ወይም የከሰረ ሰው፡፡

3. አንድ የኮሚሽኑ አባል የሙሉ ጊዜ ወይም የከፊል ጊዜ አባል ሆኖ ሊመደብ ይችላል፤

4. አንድ የኮሚሽኑ አባል ምደባ የሚቋረጠው፦

ሀ) በቅጥር ወይም በሌላ ሁኔታ በታክስ ሠራተኛነት ማገልገል ሲጀምር፣

ለ) ከታክስ ማጭበርበር ወይም ስወራ ጋር በተገናኘ በታክስ ሕግ መሠረት ቅጣት ከተጣለበት ወይም በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፤

ሐ) በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፣

መ) ከስሮ እዳውን ያልከፈለ ሲሆን፤

ሠ) ምደባውን ለሰጠው አካል የጽሑፍ መልቀቂያ ጥያቄ በማቅረብ ሥራውን ሲለቅ፤

ረ) የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ እና በድጋሚ ያልተመደበ እንደሆነ፤ ወይም

ሰ) የኮሚሽኑን ሥራ ለመሥራት ባለመቻሉ ወይም በተረጋገጠ የሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት በጽሑፍ በመደበው አካል ከሥራው ሲነሳ፡፡

5. ማንኛውም የኮሚሽኑ አባል በዚህ ክፍል መሠረት ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት በፈጸመው ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

15. **የኮሚሽኑ የአሠራር ሥርዓት እና የአባላት ክፍያ**

1. በየአስተዳደር እርከን የተቋቋመው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ የታክስ ይግባኝ ችሎት ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡ እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ከቋሚ የኮሚሽኑ አባላት በሰቢሳቢነት የሚመራውን አካል ይወክላል፡፡
2. የኮሚሽኑን የአሰራር ሥርዓትን የሚመለከት ክልል አቀፍ ተፈጻሚነት ያለው መመሪያ በክልል ማዕከል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል ተዘጋጅቶ በርዕሰ መስተዳደሩ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የኮሚሽኑ አባል በሚያየው ማንኛውም ጉዳይ በአባልነቱ ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ሊጋጭ የሚችል ቁሳዊ፣ የገንዘብ፣ ወይም ሌላ ጥቅም ሲኖር ይህንኑ ጥቅም ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ መግልጽ ያለበት ሲሆን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊም ይህንን ጥቅም በመመዝገብ አባሉ በይግባኝ ሰሚነት እንዳይሳተፍ ያደርጋል፡፡
4. የኮሚሽኑ ቋሚ ወይም ተለዋጭ አባል የሚሆኑ ሰዎች የሚከፈላቸውን ክፍያ በሚመለከት ክልል አቀፍ ተፈጻሚነት ያለው መመሪያ በክልል ማዕከል ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት በኩል ተዘጋጅቶ በርዕሰ መስተዳደሩ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

16. **ኮሚሽኑን ስለማስተዳደር**

1. በየደረጃው የሚገኝ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ የኮሚሽኑን መደበኛና አስተዳደራዊ ሥራዎችን ይመራል፤ በተለያዩ አካላት ዘንድ ኮሚሽኑን ይወክላል፡፡
2. የክልል ማዕከል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በየአስተዳደር እርከን ለሚገኘው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሬጅስትራር እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች የሚሟሉበትን ጥያቄ ለርዕሰ መስተዳደር እያቀረበ በሚያጸድቀው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::

17. **የኮሚሽኑ የፋይናንስ ምንጭና አሠራር**

1. የኮሚሽኑ በጀት በክልሉ መንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
3. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር ኦዲት ይደረጋሉ፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Central Ethiopia Regional State Office of the President

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ
Central Ethiopia Region State Justice Bureau

18. **የኮሚሽኑ ዓመታዊ ሪፖርት**

1. በየአስተዳደር እርከን የሚገኘው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ኮሚሽኑ ተጠሪ ለሆነበት የአስተዳደር እርከን እና አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለበጀት ዓመቱ የተዘጋጀው ሪፖርት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክልል አቀፍ የሆነ ሪፖርት በክልል ማዕከል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጽ/ቤት አማካይነት ለርዕሰ መስተዳደሩ ይቀርባል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

<u>ኮሚሽኑ በይግባኝ ሰሚ ሂደት ያለው ሥልጣን</u>

19. **የኮሚሽኑ ሥልጣን**

1. ኮሚሽኑ፣
   ሀ) ማስረጃ በቃለ መሃላ ወይም በማረጋገጫ መቀበል፣
   ለ) የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ይግባኝ ሰሚ ሂደቱ ማስታወቂያ በአግባቡ ደርሶት ያልቀረበ ወገን በሌለበት የስሚ ሂደቱን መቀጠል፣ ወይም
   ሐ) የስሚ ሂደቱን በቀጠሮ ማስተላለፍ ይችላል፡፡
2. የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ ሰሚ ሂደት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
3. በኮሚሽኑ የሰሚ ሂደት እንደ ምስክር ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ሰው በኮሚሽኑ መመሪያ መሠረት በክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለተጠራ ምስክር የሚከፈለው ያህል የውሎ አበል ክፍያ ይፈጸምለታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት

የኮሚሽኑ ውሳኔ

20. **የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቋረጥ፣ስለመዝጋት ወይም እንደገና ስለማየት**

1. ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለኮሚሽኑ ያቀረበውን ይግባኝ በማናቸውም ጊዜ ለኮሚሽኑ ሬጅስትራር የጽሑፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ማቋረጥ ወይም መተው የሚችል ሲሆን፣ ኮሚሽኑም ይህ በሚሆንበት ጊዜ ይግባኙን ይዘጋል።
2. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት በአካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ይግባኙን መዝጋት ይችላል።
3. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከይግባኙ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ሰብሳቢው ስለኮሚሽኑ ሆኖ ይግባኙን መዝጋት ይችላል።
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት ይግባኙን የዘጋ እንደሆነ፣ይግባኝ ባዩ የይግባኙ መዘጋት ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኙ እንደገና እንዲታይለት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል።
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፣ በኮሚሽኑ ሰብሳቢ የሚሰጥ ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ይግባኙን እንደገና ሊያይ ይችላል።

21. **በተከራካሪ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ስምምነት**

በይግባኙ ሰሚ ማንኛውም ደረጃ ከይግባኙ ወይም ከይግባኙ ከፊል ጉዳይ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ ስለሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ የተስማሙ እንደሆነ፣

1. ስምምነት የተደረሰው ኮሚሽኑ ከሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በሁኔታዎቹ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።
2. ስምምነት የተደረሰው በይግባኙ ከፊል ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በይግባኙ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የስምምነቱን ሁኔታዎች ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት Central Ethiopia Regional State Office of the President

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ Central Ethiopia Region State Justice Bureau

22. **ለቢሮ ስለሚመለስ ውሳኔ**

1. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 89 መሠረት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ እንደገና እንዲመለከተው ለቢሮው ሲመልስ፣ ቢሮው ኮሚሽኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ከግምት በማስገባት፣

   ሀ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማጽናት፣

   ለ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማሻሻል፣ ወይም

   ሐ) የአዋጁ አንቀጽ 89(6) ተፈጻሚ ሲሆን የታክስ ስሌቱን ከፍ ማድረግን ጨምሮ ይግባኝ የሚባልበትን ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት ይችላል::

2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ሲያሻሽል ወይም አዲስ ውሣኔ ሲሠጥ የተሻሻለው ወይም የተሰጠው አዲስ ውሳኔ በኮሚሽኑ በይግባኝ እየታየ እንዳለ ይግባኝ የሚቀርብበት ውሳኔ የሚቆጠር ሲሆን፣ይግባኝ ባዩ ባቀረበው ይግባኝ ሊቀጥል ወይም ይግባኙን ሊያነሳ ይችላል::

23. **ውሳኔ ስለማረም**

1. ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሠረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል::
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሻሻለው ይዘት በኮሚሽኑ እንደተሰጠ ውሳኔ ይቆጠራል::
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፣

   ሀ) የህትመት ወይም የአጻጻፍ ስህተትን፣ ወይም

   ለ) በውሳኔ እና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይ ማንኛውንም አለመጣጣም ይጨምራል::

ምዕራፍ አራት

<u>የኮሚሽኑ አስተዳደር</u>

24. **የይግባኝ ሰሚ የሚካሄድበት ቦታ**

የኮሚሽኑ የክርክር ስሚዎች የኮሚሽኑ ሰብሳቢ በሚወስነው ቦታ ይካሄዳሉ:: ስለሆነም የይግባኝ ሰሚ የሚካሄድበትን ቦታ ኮሚሽኑ ለተከራካሪዎች ማሳወቅ አለበት::

25. **ወጪዎች**

ተከራካሪዎች በክርክሩ ሂደት ያወጡትን ወጪን በሚመለከት ኮሚሽኑ ተገቢ እና ምክንያታዊ መስሎ የሚታየውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

26. **ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ስለማቅረብ**

ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚገባ ማንኛውም ሰነድ በኮሚሽኑ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት፡፡

27. **ሰነዶች የሚሰጡበት አድራሻ**

ይግባኝ ባይ ከይግባኙ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ማንኛውም ሰነድ አድራሻውን በጽሑፍ ማስታወቂያ ለሬጅስትራሩ መስጠት አለበት፡፡

ክፍል ስምንት

ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

28. **የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ስለመሆን**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆነ ሰው ይቆጠራል፡፡

   ሀ) በታክስ፣ በሂሣብ አያያዝ፣ በንግድ ሥራ፣ በሕግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ከዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ማስረጃ ያለው እንደሆነ፣ እና

   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት፣

   (1) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት፤ ወይም

   (2) እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል፤ ወይም የሁለት ዓመት የሙሉ ጊዜ የሥራ ልምድ ያለው እንደሆነ፡፡

2. አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) ከተመለከተው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ልምድ በሌላ ሀገር ያገኘ እንደሆነ ቢሮው ግለሰቡ የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) መስፈርት እንዳሟላ አድርጎ ሊወስደው ይችላል፡፡
3. የሚከተሉት ግለሰቦች የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው አይቆጠሩም፡፡

ሀ) ዕዳውን መክፈል ያልቻለ መክሰሩ በፍርድ የተረጋገጠ ግለሰብ፤

ለ) በስነ-ምግባር ጉድለት በሙያ ማህበር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ፤

ሐ) ከእምነት ማጉደል ጋር በተገናኘ ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ እና ቅጣቱን ፈፅሞ ያልተሰየመ ግለሰብ፤

መ) በተሻረው አዋጅ ጭምር የታክስ ግዴታውን ያለመወጣት ሪከርድ ያለበት ግለሰብ፤

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29. ***የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች***

1. በተሻረው አዋጅ መሠረት የተቋቋመው **"የታክስ ይግባኝ ጉባኤ"** አባል የነበሩ ሰዎች አገልግሎት በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት **"የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን"** በክልሉ በየአስተዳደር እርከን ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር ይቋረጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተገለጸው መሠረት የታክስ ይግባኝ ጉባኤ አባል የነበረ ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሠረት ለአዲሱ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊመደብ ይችላል፡፡
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 14(2)(ለ) "የታክስ ሕግ" በሚል የተጠቀሰው የተሻረውን አዋጅ ይጨምራል፡፡
4. ለቀድሞው የታክስ ይግባኝ ጉባኤ የቀረበ ይግባኝ፣ ጉባኤው ሥራውን ከማቆሙ በፊት ውሳኔ ያላገኘ እንደሆነ፣ የአዲሱ ኮሚሽን ሰብሳቢ የሚሰጠው ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኙ በአዲሱ ኮሚሽን ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Central Ethiopia Regional State Office of the President
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Justice Bureau

30. **መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላሉ፡፡

31. **ደንቡ የሚጸናበት ቀን**

ይህ ደንብ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት መስተዳድር ም/ቤት ፀድቆ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ከቀን ….ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሆሳዕና

መስከረም 23 ቀን 2017 ዓ.ም

እንዳሻው ጣሰው

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳደር